# ሦስት ዓመት በሀዘን

ሦስት ዓመታት፥ ሦስት ወራት፥ ሦስት ደቂቃ፥
አልቆመም የእኛ ሀዘን ሰቆቃ፥
ማጣት አባት ወንድም አለኝታ፥
አለቀነሰ  ጨመረ ሀዘናችን በረታ ።
ሣሙኤል የወገን ተስፋ፥
ተደበቀብን ከፊታችን ጠፋ።
እንረሳህ ሣሙኤል ተስፋችን፥
እምባ ቢደርቅ ከዓይናችን፥
ልብ ያለቅሳል ተራ ይዞ፥
አያልቄ ነው የሀዘን ጎዞ ።
አልራራልን  ከአምና ዘንድሮ፥
ያለፀባዩ ክፋት ተምሮ፥
ላይመለስ ጨከነ ቆርጦ በቃ፥
ሦስት ዓመታት ሙሉ ይኸው አልነቃ፥
ሞት ወስዶብን ሣሙኤልን ከኛ፥
ለዓላማ ጽኑ ለደግ አልተኛ፥
የማያዳላ ክፉ ቀማኛ፥
አባት ነህ ወንድም የበላይ ሣሙኤል፥
የፍቅር አድማስ የማይደርቅ ተክል፥
የልብ ፋኖስ የበጎ መሪ፥
ሠላምን አንጋሽ አስተባባሪ፥
ቦታውን ቢለቅ በጋ ለክረምት፥
ታህሣሥ ለኛ ሁሌ ሙት ዓመት፥
የሚግል ሀዘን የማይጠፋ እሳት፥
ቅስም የሚሰብር ናፍቆትህ እንፋሎት።

ከቤተሰብ

--------------//////////-------------